**የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት**
**The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order**
www.ethiopianorthodox.org

## ማጠቃለያ

**ከላይ በአጭሩ ከተገለጹት ትምህርቶች መሐከል የሚከተሉት ሰባቱ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን በመባል ይታወቃሉ። እነርሱም፤**
1ኛ/ **ምስጢረ ጥምቀት**
2ኛ/ **ምስጢረ ሜሮን**
3ኛ/ **ምስጢረ ቁርባን**
4ኛ/ **ምስጢረ ንስሐ**
5ኛ/ **ምስጢረ ክህነት**
6ኛ/ **ምስጢረ ተክሊል**
7ኛ/ **ምስጢረ ቀንዲል**

**ጥያቄ፤**-**ከእነዚህ ከሰባቱ ምስጢራት መካከል የማይደገሙት ማለት በድጋሚ የማይፈጸሙት የትኞቹ ናቸው?**

አንድ ጊዜ ከተፈጸሙ በኋላ የማይደገሙ ምስጢራት፥
1ኛ/ ምስጢረ ጥምቀት
2ኛ/ ምስጢረ ሜሮን
3ኛ/ ምስጢረ ክህነት
4ኛ/ ምስጢረ ተክሊል ናቸው።

እነዚህ ሦስቱ ምስጢራት፤ ሕገ ቤተክርስቲያን በሚያዘው መሠረት ከተፈጸሙ በኋላ በምንም ዓይነት እንደገና አይፈጸሙም። ይህም ማለት ሓዋርያዊትና ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን በምታዘው ሥርዓተ ሐዋርያት መሠረት አንድ ጊዜ የተጠመቀ ሰው ድጋሚ መጠመቅ አይገባውም። ጥምቀት አንዲት ናትና (ኤፌ. 4፤5)። ሥልጣነ ክህነትም አንድ ጊዜ ከተቀበሉት በኋላ በድጋሚ ሊቀበሉት አይቻልም። ሥልጣነ ክህነት ከፈረሰ በኋላ እንደገና አይሠራም፣ አይጠገንም።

**ጥያቄ፤-ምስጢራተ ቤተክርስቲያን ለምን ሰባት ብቻ ሆኑ?**
በቅዱስ መጽሐፍ አቆጣጠር ሰባት (7) ፍጹምና ሙሉ ቁጥር በመሆኑ ከአንድ እስከ ሰባት (1-7) የተዘረዘሩት ምስጢራተ ቤተክርስቲያንም እንከንና ጉድለት የሌለባቸው ፍጹማን ናቸው። ሰባት ቁጥር በመጽሐፍ ቅዱስ ሥርዓት ፍጹም ለመሆን ለማወቅ ከዚህ የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመልከት፤
1ኛ/ እግዚአብሔር የፈጠራቸው ከእሑድ እስከ ቅዳሜ ያሉት ቀኖች (ዕለታት) ሰባት ናቸው (ዘፍ. 1፤5-31፤ 2፣1-4)

2ኛ/ ከአዳም ሰባተኛ ትውልድ የሆነው ሄኖክ ሞትን ሳይቀምስ ቀርቶአል። በሕይወተ ሥጋ ሳለም እግዚአብሔር ወደ እርሱ ወስዶታል (ሰውሮታል) (ዘፍ. 5፤21-24)

3ኛ/ የእግዚአብሔር ሰው ኖኅ በመርከብ ውስጥ ሆኖ ምድርን ያጥለቀለቃት የጥፋት ውኃ ጎድሎ እንደሆነ ታረጋግጥለት ዘንድ ርግብን ላካት። እርሰዋም ውኃው ያልጎደለ መሆኑን በ ማረጋገጥ ወደ ኖኅ ተመለሰች። ከዚያም ሰባት ቀን ቆይቶ ርግቢቱን መልሶ ሰደዳት። ርግ ብም በማታ ጊዜ በአፍዋ ለምለም የወይራ ቅጠል ይዛ ተመለሰች። ኖኅም ከምድር ላይ ው ኃው እንደቀለለ (እንደ ጎደለ) ተገነዘበ። እንደገናም ሰባት ቀን ቆይቶ ርግቧን ላካት፤ ርግ ቢቱ ግን ዳግመኛ ወደ ኖኅ አልተመለሰችም። በዚህም ምክንያት ጻድቁ ኖኅ ውኃው እንደ ደረቀ ተገንዝቦ ከመርከብ ወጣ (ዘፍ.8፤ 6-12)።

የእግዚአብሔር ሰው ኖኅ ሰባት ቀን እየቆየ ርግቢቱን መላኩ ቁጥር ሰባት ፍጹምና ጥልቅ ትርጉም ያለዉ መሆኑን የሚያመለክት ነው።

4ኛ/ ሰባት ቁጥር ጥልቅ ትርጉም ያለው ፍጹም ቁጥር መሆኑን የተገነዘበው ቅዱስ ዳዊት «ስ ብዓ ለዕለትየ እሴብሐከ በእንተ ኩነኔ ጽድቅከ»፤ «ስለ ጽድቅህ ፍርድ በቀን ሰባት ጊዜ አ መሰግንሃለው» ብሎአል (መዝ.118፤ 164)

5ኛ/ ሰባት ቁጥር ፍጹምና ዐቢይ ትርጉም ያለው መሆኑ ይታወቅ ዘንድ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥ ሮስ ወደ ጌታችን ቀርቦ (ጌታ ሆይ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት? እስከ ሰባት ጊዜ ነውን? አለው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን እስከ ሰባት ጊዜ ሰባ እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ ብቻ አልልህም» ሲል መለሰለት(ማቴ. 18፤21)።

6ኛ/ጌታችን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ በፈቃዱ ነፍሱን ከሥጋው ከመለየቱ ማለትም ከመለየ ቱ በፊት በመልዕልተ መስቀል (በመስቀል ላይ) እንዳለ ሰባት ጊዜ ተናግሯል ይኸውም፤

ሀ. አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው? ብሎ ለሰቀሉት ጸ ልዮላቸዋል (ሉቃ. 23. 34)።

ለ. በቀኙ በኩል ተሰቅሎ ለነበረው ወንበዴ «እውነት እልሃለው ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ» ብሎታል (ሉቃ. 23፤ 43)።

ሐ. ዘጠኝ ሰዓትም በሆነ ጊዜ ጌታ ኢየሱስ «ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ ብ ሎ በታላቅ ድምጽ ጮሆአል» (ማቴ. 27፤ 46)።

መ. ጌታችን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ፤ እናቱንና ደቀ መዝሙሩን በመስቀ ል አጠገብ ቆመዉ ባያቸው ጊዜ እናቱን «አንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ አላት »፤ ደቀ መዝሙሩንም «እንኋት እናትህ» አለው (ዮሐ. 19፤25-27)።

ሠ. «ከዚያ በኋላ ጌታ ኢየሱስ አሁን ሁሉ እንደ ተፈጸመ አውቆ የመጽሐፉ ቃል ይፈጸም ዘንድ «ተጠማሁ» አለ (ዮሐ. 19፣28)።

ረ. ከዚያ በኋላ «ሁሉ ተፈጸመ» አለ (ዮሐ. 19፣30)።

ሰ. በመጨረሻ ጌታችን እግዚአብሔር አብን «አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደ ራ እሰጣለው» ብሎ ነፍሱን ሰጠ (ሞተ) (ሉቃ. 23፤46-47)

እነዚህ ከዚህ በላይ የተመለከቱት ኃይለ ቃሎች ጌታችን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ የተናገራቸው ሲሆኑ፤ በሊቃውንት አባባል «ሰባቱ አጽርሐ መስቀል» በሚል ይጠራሉ። በዚሁም ላይ ጌታችን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ በፈቃዱ ከመሞቱ በፊት ሰባት ጊዜ መናገሩ ሰባት ፍጹም ቁጥር መሆኑን ያመለክታል።

ይልቁንም ምስጢራተ ቤተክርስቲያን ሰባት የሆኑበት ምክኒያት በግልጽ የሚያስረዳ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አለ። እርሱም በምሳሌ ሰሎሞን ምዕራፍ ዘጠኝ ላይ ተመዝግቦ ይገኛል፤ ቃሉም «ጥበብ ቤትዋን ሠራች፤ ሰባቱም ምሶሶችዋን አቆመች። ፍሪዳዋን አረደች፤ የወይን ጠጅዋን ደባለቀች፤ ማዕድዋም አዘጋጀች» የሚል ነው (ምሳ. 9፤1-3)።

ጥበብ በምሳሌ ሰሎሞንም ሆነ በሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት በሴት አንቀጽ (በሴት ጾታ) መጠራትዋ የታወቀ ቢሆንም በትክክለኛው ምስጢራዊ ምሳሌ በምዕራፍ ስምንትና ዘጠኝ ላይ የተመዘገበው ታሪክ ስለጌታችን መሆኑ የታወቀ ነው.። ሰባቱ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን ገልጸ ለሰው ልጆች የሰጠውም ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ በየምዕራፉ ተገልጿል።

ስለዚህ ሓዋርያዊት ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን ሰባቱን ምስጢራት፤ ከጌታችንና ከቅዱሳን ሐዋርያት ተቀብላ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ ስትጠብቃቸውና ስትሠራባቸው (ስትፈጽማቸው) ትኖራለች።

ትምህርተ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት ከሚለው አቡነ ገብርኤል በ1991 ካሳተሙት የተወሰደ።

## <u>ምስጋና</u>

በዚህ ዌብ ሳይት ላይ የተጻፉትን ምስጢራተ ቤተክርስቲያን «ከትምህርተ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት» መጻሕፍ ላይ እንዲሁም በልዩ ልዩ ርዕሶች ላይ ለመናፍቃን መልስ የተሰጠባቸውን «ክብረ ቅዱሳን» ከሚለው ኮፒ አድርገን ብዙሃን ትምህርት ያገኙበት ዘንድ እንድንጠቀምበት ለፈቀዱልን ለብፁዕ አቡነ ገብርኤል ከልብ የመነጨ ምስጋና እናቀርባለን።

ብፁዕ አባታችንን እግዚአብሔር በሕይወትና በመልካም ጤና ይጠብቅልን።